የሰ/መ/ቁ 39543

ግንቦት 4 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሠ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** የፍልውሃ አገልግሎት ድርጅት ነ/ፈጅ ካሣሁን ወርቁ - ቀረበ

**ተጠሪ፡-** አቶ በረከት ተ/ማሪያም - ቀርቧል

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን ተጠሪ የሥር ከሣሽ አመልካች ተከሣሽ ነበሩ፡፡ ተጠሪ ባቀረቡት ክስ በአመልካች ድርጅት ሰራተኛ መሆናቸውን ጠቅሰው አመልካች የሥራ ውሌን ያለአግባብ ስላቋረጠብኝ ወደ ሥራዬ ይመልሰኝ ካልሆነ በሕጉ የተቀመጡትን ክፍያዎች ይክፈለኝ ሲል ጠይቋል፡፡

አመልካችም ለክሱ በሰጠው መልስ ተጠሪ ሊሰናበቱ የቻሉት አድራሻ የሌለውና ለማስረጃነት ብቁ ያልሆነ የሥራ ልምድ ማቅረባቸው በመረጋገጡ ነው፡፡ ስለዚህ ስንብቱ ሕጋዊ ነው በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡

የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም የቀረበለትን ክስ ግራ ቀኙ ባቀረቡት ክርክር አግባብነት ካለው ሕግ ጋር በማገናዘብ መርምሮታል፡፡ በዚህም መሠረት አመልካች በ26/5/2000 በፃፈው ደብዳቤ ተጠሪ ያቀረቡትን የምስክር ወረቀትን አስመልክቶ ድርጅቱ ተጠይቆ የአይስክሬም ሽያጭ በድርጅቱ እንደማይካሄድ ቢገልፅም፤ አመልካች ተገቢውን አካል መጠየቁንና ሰርቷል የተባለበትን ጊዜ አይገልፅም፣ ማስረጃው ትክክል አልነበረም እንኳ ቢባል በአሰሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁ 377/96 አንቀጽ 27(1)(ሐ) መሠረት በሥራ ላይ ተፈፀመ የተባለው ማጭበርበር ድርጊት ሊባል የሚችለው ከቅጥር በኋላ ሰራተኛው ስራውን በሚያከናውንበት ወቅት የሚፈፅማቸውን የማጭበርበር ድርጊቶችን ነው፡፡ በመሆኑም የተፈፀመው ድርጊት በዚህ አንቀፅ ሥር የሚወድቅ ስላልሆነ ስንብቱ ህገ ወጥ ነው፡፡ በአዋጅ አንቀፅ 43(2)(5) መሠረት የሁለት ወር ደሞዙ ተከፍሎት ተጠሪ ወደ ሥራቸው ይመለሱ ሲል ወስኗል፡፡

ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለትም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 337 መሠረት መዝገቡን ዘግቷል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡ አመልካች ሐምሌ 22/2000 ዓ.ም ፅፈው ባቀረቡት አቤቱታ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት እና በከፍተኛው ፍ/ቤት የተሰጡት ውሣኔዎች መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ሲል እንዲታረምለት ጠይቋል፡፡

ይህ የሰበር ችሎትም አቤቱታውን መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርቦ ክርክራቸውን ሰምቷል ጉዳዩ በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው የተጠሪ ስንብት ሕገ ወጥ ነው የሁለት ወር ደሞዝ ተከፍሎት ወደ ሥራ ይመለስ መባሉን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ነው፡፡ በዚህም መሠረት የግራ ቀኙ ካሰሙት ክርክር አቤቱታው የቀረበበትን ውሣኔ አግባብ ካለው ሕግ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

የጉዳዩን አመጣጥ ባጭሩ ስናይ የአመልካች ድርጅት ተጠሪን ሲያሰናብት መሠረት ያደረገው በሀሠተኛና ብቃት በሌለው ማስረጃ (የምስክር ወረቀት) በማቅረብ የተቀጠረ መሆኑን ባደረገው ማጣራት ደረስኩበት ሲል በማሰናበቱ ምክንያት የሥር ፍ/ቤቶችም ጉዳዩን በማከራከር ተጠሪ ፈፅመዋል የሚባል ድርጊት እንኳ ቢኖር በአዋጅ 377/96 አንቀጽ 27(1/ሐ) ሥር ሊወድቅ አይችልም በሥራ ላይ እያሉ የፈፀሙት ማጭበርበር አይደለም፣ ስንብቱ ህገ ወጥ ነው፣ ተጠሪ የሁለት ወር ደሞዝና ወደ ሥራ ሊመለሱ ይገባል ሲል ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

በዚህ ጉዳይ የሥር ፍ/ቤቱ ስንብቱ ሕገ ወጥ ነው ሲል መሠረት ያደረገው የአዋጁን አንቀፅ 27(1/ሐ) በመጥቀስ ትርጉም በመስጠት የተጠሪ ድርጊት በሥራ ላይ እያሉ የተፈጠረ አይደለም ሲል ነው፡፡ የአዋጁ አንቀፅ 27(1/ሐ)"ን" ሙሉቃል ስናነብ "የሥራ ውልን ያለማስጠንቀቂያ ማቋረጥ የሚቻለው ሠራተኛው በሥራው ላይ የማታለል ወይም የማጭበርበር ተግባር ሲፈፀም ነው" ይላል፡፡ በመሆኑም የዚህን አንቀፅ ትርጉምና ተጠሪ የፈፀሙትን ማጤኑ አስፈላጊ ነው፡፡ ከመጀመሪያው አመልካች የስንብቱን ምክንያት ሲገለፅ ተጠሪ ባቀረቡት የሐሰት ማስረጃ መቀጠራቸውን የተጠራጠረው ተጠሪ በተቀጠሩበት የአይስክሬም ስራ ብቃት ስላጡና ደንበኛም እየቀነሰ በመምጣቱ እና ባደረገው የማጣራት ሥራ ማስረጃው ለተጠሪ ሰጠ ያለውን ድርጅት በግንባር በመሄድ በድርጅቱ አይስክሬም እንደማይሠራ በማረጋገጥ ነው፡፡ ስለዚህ ከዚህ መረዳት የሚቻለው ተጠሪ ያቀረቡት ማስረጃ በጥርጣሬ ውስጥ የወደቀ መሆኑን ነው፡፡

ባጠቃላይ ተጠሪ ከመጀመሪያውኑ ሲቀጠሩ በሐሰት ማስረጃ እስከሆነና በዚህም ማስረጃ ሥራቸውን መስራት ከጀመሩ በኋላ በመሀከሉ የማጭበርበር ድርጊት መፈፀማቸው እስከተደረሠባቸው ድረስ ይህ ድርጊት ተጠሪ በሥራቸው ላይ (ስራቸውን በማከናወን) እያሉ የፈፀሙት ነው ተብሎ ከመተርጎም ውጪ እንደ የሥር ፍ/ቤት አባባል በተቃራኒው ሊተረጐም የሚገባው አይደለም፡፡ በመጨረሻም ከግራ ቀኝ ክርክር ልንገነዘብ እንደቻልነው ማስረጃ ሰጠ የተባለው ድርጅት የአይስክሬም ሥራ (ሽያጭ) የማይከናወንበት መሆኑ ስለተረጋገጠ የተጠሪ ማስረጃ የተጭበረበረ ለመሆኑ በጥያቄ የሚገባ አይደለም፡፡

ስለዚህ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከላይ የተጠቀሱትን ነጥቦች ሣያገናዝብ ለአንቀጽ 27(1/ሐ) አግባብ ያልሆነ ትርጉም በመስጠት ስንብቱ ህገወጥ ነው ሲል፤ የከፍተኛው ፍ/ቤትም ይግባኙን መዝጋቱ መሠረታዊ የህግ ሥህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 24723 ቀን 4/10/2000 እና የከፍተኛው ፍ/ቤት በመ.ቁ 68331 በቀን 17/11/2000 የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. ስንብቱ ሕጋዊ ነው፡፡ ተጠሪ የሁለት ወር ደሞዝ መከፈሉም ሆነ ወደ ሥራ ሊመለሱ አይገባም ብለናል፡፡
3. የግራ ቀኝ ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ